**መንገዶቻችን!**

ከድንበሩ ወሰኔ

ዋሽንግተን - ዲሲ

*የነዚህ ተቃዋሚ ነን ባዮች ነገር አሁንስ ግራ ገባን:: ይኸ ቅጥ አንባሩ የጠፋ የተቃውሞና የትግል ስልታቸው ቀድሞም ቢሆን መልክ ያለው አልነበረም፣ አሁንም ብሶበት ቀጥሏል::*

*ዓለም በፈጣን የለውጥ ባቡር እየከነፈ ባለበት በዚህ ዘመን እነዚህ ወገኖች ለምን እንደግመል ሽንት ወደኋላ ብቻ ለመሄድ እንደተፈረደባቸው አይገባንም::*

*ኢትዮጵያውያን ከብዙ ዘመን ታሪካችን ብዙ ለመማር ዕድል አግኝተናል:: ወደፊት ሊያራምደን ወይም ወደኋላ ሊመልሰን፣ ሊገነባን ወይም ሊያፈርሰን፣ ሊያከብረን ወይም ሊያዋርደን፣ ሊያፋቅረን ወይም ሊያለያዩን የሚችለው መንገድ ሀሳብና አማራጭ የትኛው እንደሆነም ለይተናል::*

*በመፅሐፍ ቅዱስ እንደምናነበው በዘመኑ በነበሩት ሰዎች ሐጢያት ምክንያት እግዚአብሔር ተቆጥቶ የሶዶም ከተማን ሊያጠፋ ሲወስን ሎጥና ቤተሰቦቹ በመልካም ሥራቸው የተመረጡ ነበሩና ከከተማው እንዲያወጡዋቸው መላዕክት ወደ እነርሱ ተላኩ::*

*የእግዚአብሔር መላዕክት ሎጥና ቤተሰቦቹን ከከተማው ለማውጣት ጥቂት መንገድ እየመሩ ከወሰዷቸው በኋላ አንድ ነገር እንዳያደርጉ አስጠንቅቀዋቸው ነበር:: ጥለውት ወደወጡት ዝሙት፣ ርኩሰት፣ በደል ወደሞላበት ከተማ ዞረው እንዳይመለከቱ::*

*ታላቁ ሰው ሎጥና ሁለት ልጆቹ የተሰጣቸውን ምክር ሰምተው ወደፊት በመሄዳቸው ሲድኑ የሎጥ ሚስት ልብ ግን ከዚያ የሐጢያት ኑሮ ለመላቀቅ አልቆረጠም ነበርና ወደነበረችበት ወደኋላ ዞራ ስትመለከት የጨው አምድ ሆና ቀርታለች::*

*ይኸ በመፅሐፍ ቅዱስ ያለ ታሪክ ነው::*

*ኢትዮጵያውያን ለዘመናት ከነበርንበት ጥልቅ የድህነትና የኋላቀርነት አዘቅት ለመውጣት ጉዞ ጀምረናል:: ከነበርንበት አስከፊ ሁኔታ በአስተማማኝ መውጣት የምንችለው በቁጭትና በቁርጠኝነት ወደፊት ስንሄድ ብቻ ነው:: በምንም ምክንያት ወደነበርንበት ወደኋላ የመመለስ ዝንባሌ ቢኖረን ኪሣራ እንጅ ትርፍ አይሆንም::*

*ምርጫችን አንድ ነው:: ምርጫችን ጥለነው ወደ ወጣነው የርሃብ ድህነትና ኋላቀርነት፣ የርስ በርስ ጥላቻ ግጭትና ንትርክ ሥርዓት መመለስ አይደለም:: ምርጫችን ተቻችለን፣ ተከባብረንና እጅ ለእጅ ተያይዘን ለልጅ ልጆቻችን በክብር የምናወርሳት ያደገች የበለፀገች እኩልነት ሠላምና ፍቅር የሠፈነባት አዲሲቱን ኢትዮጵያ እውን ማድረግ::*

*ሀገሬን ወገኔን እወዳለሁ የሚል ማንም ቢኖር እርሱ ከግል ስሜት፣ ፍላጎትና ምኞቱ ይልቅ ሀገሩን ያስቀድም::*

*ሠላም ፍቅርና ብልፅግና የሰፈነባት አዲሲቱን ኢትዮጵያ እውን ማድረግ የሚለው ብሔራዊ ዓላማና ራዕይ ከእኔና ግላዊ ስሜት በላይ እጅግ የላቀ ዘላለማዊ ጉዳይ ነው ብሎ ሊያስቀድም ስፈልጋል::ይህ ከምንምና ከማንኛችንም በላይ ነውና::*

*በሀገር ግንባታ ብሔራዊ ጉዳይ እያንዳንዳችን ቀጥተኛ ድርሻ ያለን መሆኑ አያጠራጥርም:: ድርሻን መወጣት ለማንም የማይተው የእያንዳንዳችን የሞራልና የህሊና ግዴታ ነው::*

*እኔ ምን እያደረግሁ ነው?*

*በተጀመረው የኢትዮጵያ ህዳሴ ጉዞ እኔ በተሰጠኝ መክሊት ለማትረፍ ከወገኔ ጋር ወገንኩ? ወይስ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ከዚህ በተፃራሪ ከተሰለፉ ጋር ቆምኩ? ነው ወይንስ ይህ ጉዳይ እኔን አይመለከትም ብዬ አርፌ ተቀመጥኩ? ጥያቄውም መልሱም ለእኛው ህሊና ዳኝነት የሚተው ይሆናል።*

*የበኩልን አንድ ጠጠር በመጣል ትውልድ የሚሰራው የታሪክ አካል መሆን የተቀደሰና የሚያኮራ በአፀደ ሥጋ ብቻ ሳይሆን በአፀደ ነፍስ የሚያስመሰግን የመሆኑን ያህል ይህን የሰው ልጅነት ተግባር ሳይፈፅሙ ማለፍ የሚያተርፈው ነገር ዘላለማዊ የትውልድና የህሊና ወቀሳ ብቻ ነው።*

*የሀገራችን ህዝብ የቀደመ የድህነት ታሪኩን ሊቀይር በአንድ መስመር እንደጅረት በመፍሰስ ላይ ይገኛል። ጅረቱ ኃይልና ጉልበት ያለው በመሆኑ ማንምና ምንም ሊገታው አይችልም። በተለያዩ ጊዜያት ሊገዳደሩት የሞከሩ የውስጥም የውጭም ኃይሎች ማዕበሉን ሊቋቋሙ አልተቻላቸውምና ተንገዋለው ሲጣሉ፣ ተንኮታኩተውም ሲወድቁ አስተውለናል።*

*የእህል ውሃ ጉዳይ ሆኖ ከሀገራችን ርቀን በውጭ ሀገራት የምንኖረውም ኢትዮጵያ የሁላችን ናትና በቅንነት ለሀገራችን መቆም ይኖርብናል።*

*በስደት ኖሬ በስደት ህይወት ሳይደላኝ ይህችን ምድር አልሰናበትም አንድ ቀን ወደሀገሬ እመለሳለሁ እያልን በተስፋ ያለን ብዙ ነን። ይህ ተስፋ እውን ሆኖ ልንኖርባት ለምንሻው ሀገር እድገት መስራት ለማንም የሚተው ተግባር አይደለም የእኛው ሥራ ነው።*

*ሁላችንም ሀገራችንን እንወዳለን። መውደድ በተግባር የሚገለፅ ነው፡ በተግባር ካልተገለፀ ከንቱ ነው። ሀገሬን ከልብ እወዳለሁ እያልን ራሳችንን የምንሸነግል ወይም አስመስለን ለመታዬት የምንሞክር ካለን ራሳችንን ልናታልል አይገባንም። ጉዳዩ የህሊናና ሞራል ጉዳይ ነውና።*

*የማይታይ ውስጣዊ የሀገር ፍቅር ስሜቱን በሚታይ ግብር የሚገልፀው ሰው ምንኛ የታደለና የተባረከ ነው? ይህ ነው ከሁላችን በላይ የሆነ ታላቅ ሰው። ተግባር ህያው ምስክር ነውና በአንድ ወቅት ያከናወነው ትልቅ ሥራ ዛሬም ነገም ወደፊትም ሲመሰክርልን ይኖራል።*

*እንዲህ ዓይነት ርዕሰ ጉዳይ ሲነሳ ሳናነሳው ማለፍ የማይኖርብን የእነዚህ በየአውራጎዳናው ያዙኝ ልቀቁኝ የሚሉትን፣ ደርሶ የሀገር ተቆርቋሪ ደርሶ የህዝብ ጠበቃ መስለው በመታየት በቁራ ጩኸታቸው ለሚያደነቁሩን አጉራ ዘለል ሀገር በቀል ሰዎች ጉዳይ ነው።*

*እነዚህ በውሸት ብቻ የተገነቡ ውሸት ልብስና ቀለባቸው የሆኑ ለእኛ ሀገር ከእኛ በላይ ብለው እየጮሁ ተግባራቸው ግን ዲያቢሎሳዊ መሆኑን በተደጋጋሚ ተግባራቶቻቸው ተረድተናል።*

*ፍርፋሪ የሚገኝ መስሎ በታያቸው ጊዜ የሀገር ሠላም ሊያናጋ ከሚሻ ባዕድ ጠላት ጋር ሳይቀር ሲሞዳሞዱና የለየለት የክህደት ተግባር ሲፈፅሙ እንደማይሰቀጥጣቸው አስተውለናል።*

*የኢትዮጵያ ህዝብ ተስማምቶና ተፋቅሮ በአንድ ልብ በአንድ ሀሳብ መቆሙ እረፍት እየነሳቸው ኢትዮጵያ ወደነግብፅ፣ ሊቢያ፣ ሶሪያ አይነት አብዮት እንድትገባላቸው ባህር ማዶ ሆነው የማያነሱት የማይጥሉትና የማያጨሱት ጭስ እንደሌለ እስኪበቃን አይተናል።*

*የቀበሮ ባህታውያን ሆነው ስለኢትዮጵያ እናንተ አይታያችሁም ብታዩም የምታዩት ትክክል አይደለም፣ እኛ እንንገራችሁ፣ እኛን ስሙ፣ እኛን ብቻ አምናችሁ ተከተሉ እያሉ ብርሃኑን ጭለማ፣ ነጩን ጥቁር፣ ያልተፈጠረውን እንደተፈጠረ፣ ያለውን እንደሌለ አድርገው በማቅረብ የነበረንን በጎ ሀገራዊ ስሜት በመሸርሸር የጥፋት ድግሳቸው አድማቂ ሊያደርጉን የሚሞክሩ የእኛው ሀገር ሰዎች ያለሐፍረት በአደባባይ ሲቆሙ ማዬት የሚያስገርምና የሚያሳዝን ነው።*

*በተለይ በዚህ በአሜሪካን ሀገር ያለን ወገኖች ይህን በቅጡ እየተገነዘብን የመጣን ቢሆንም ወቺ ጉድ እያልን አፋችንን ይዘን ከመገረም ባለፈ እረ በቃችሁ ብለን እርቃናቸውን ማዬት እንዲችሉ አልረዳናቸውም። ይኽ ደግሞ ሉጓም በሌለው ሌጣ ፈረሳቸው የሽምጥ እንዲጋልቡ የልብ ልብ ሰጣቸው።*

*የበግ ለምድ ለብሰው በበጎች መካከል ለመመሳሰስ የሚሞክሩት ተኩላዎች አሁን ጊዜው እየመሻባቸው ይመስላል። ገደብ የለሽ ውሸትና ሽፍጣቸው ተመልሶ እየበላቸውና እያባላቸውም ነው።*

*በጊዜ ውስጥ የማይማርና የማይለወጥ በህይወት የሌለ ብቻ ነውና በጭፍን የሐሰት ፕሮፓጋንዳቸው ጋጋታ ከግል ስምና ክብራቸው በላይ ላልሆነ የፖለቲካ ቁማር ጨዋታቸው መጠቀሚያ ሊያደርጉን እንደማይችሉ በግልፅ ሊነገራቸው ይገባል።*

*መንገዶቻችን እንምረጥ።*

*ለውድ ሀገራችን ዕድገት በጋራ የመስራት የሞራልና የትውልድ አደራ አለብን። ኮሪያ ያደገችው በኮሪያውያን፣ ቻይናም ያደገችው በቻይናውያን፣ ጃፓንም ያደገችው በጃፓናውያን ነውና የእኛዋም ኢትዮጵያ ያለጥርጥር በእኛው በኢትዮጵያውያን ታድጋለች። ይህ ይሆን ዘንድ እነዚህ በፈጠራ ወሬ ተጠምደው ውዥንብር ሊፈጥሩብንና እንቅፋት ሊሆኑብን የሚሞክሩ የሐሰት አቅማዳዎችን* **Stop** *ማለት ግድ ይለናል።*

*ሀገራችን የህዳሴ ጉዞዋን ጀምራለች። የሀገር ቤት ወገናችን የተሻለች ኢትዮጵያን እውን የማድረግ ራዕዩን ሊያሳካ በቁርጠኝነት ተንቀሳቅሷል። በውጭ ያለን እኛም ከእነዚህ የጥፋት አጋፋሪዎችና ዳንኪረኞች ውዥንብር ራሳችንን ነፃ አውጥተን ከወገናችን ጎን መሰለፍ አለብን።*

*ኢትዮጵያ ብዙ ረጅም በማይባል ጊዜ ያስመዘገበቸው ውጤት ቀላል የሚባል አይደለም። ይህን ማዬት የማይችሉ ወይም የማይፈልጉት ራስ አልባ የወሬ ሰዎች ሁሌም ሊያወሩልን የሚፈልጉት ከጨፈገገው ልባቸው የሚወጣውን የጥፋት ምኞትና ማለቂያ የሌለው የጨለምተኞች ሙሾ ነው።*

*ፍላጎትና ራዕያቸው የተሻለ መስራት ሆኖ አይደለም። ሌት ተቀን የሚደክሙለት ዋነኛው ዓላማቸው በማንኛውም ምክንያት ትርምስ ተፈጥሮ በዚህ መሐል እነሱን ተጠቃሚ የሚያደርግ ቀዳዳ ከተገኘ መሹለክ ሆኖ እንጅ። ከዚህ የተለዬ ዓላማና ግብ እንደሌላቸው ግልፅ ነው። ከዚህ ሌላ ምን ግብ እንዳላቸው አውቃለሁ የሚል ካለ ቢያካፍለን ለሁላችንም ሊጠቅም ይችል ይሆናል።*

*በተለይ እኛ በሰለጠነና ባደገው ዓለም የምንኖረው ኢትዮጵያውያን ሀገራችን ምን ያህል ወደኋላ የቀረች እንደሆነና ሌሎቹ ሀገራትም እንዴት እንዳደጉ የማየት ዕድል በማግኘታችን በተፈጠርንባት ሀገር ጉዳይ ከማንም በላይ ቁጭት አለብን።*

*ሀገራችን በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆና ለሌሎች መቶ አመታት መዘለቅ እንደሌለባትም እናስባለን፡ ይህ እንዲሆን ደግሞ የእያንዳንዳችን ድርሻ እንዳለንም አንዘነጋውም።*

*መንገዳችንን እንምረጥ። ሁለት መንገዶች ከፊታችን አሉ። አንደኛው መላው የሀገራችን ህዝብ የመረጠው እጅ ለእጅ ተያይዞ ከድህነት ጋር ሙሉ ጦርነት አካሂዶ ጦርነቱን በአሸናፊነት መወጣትነው። ሌላው መንገድ ደግሞ ህዝብን ከዚህ ዘመቻው ለማስተጓጎልና ለማደናቀፍ በሚረዳ ትርኪ ምርኪ ፕሮፓጋንዳ ተጠምዶ ዘመንን መግፋት ነው።*

*የልማት ኃይሉ በልማት መንገዱ ቀጥሎ በድል ላይ ድል በማስመዝገብ ላይ ነው። የጥፋት ኃይሉም በመረጠው መንገድ ተንቀሳቅሶ በእንቅፋትነትነቱና ይህች ሀገር ወደማያባራ ቀውስ አምርታ ምናልባት የሚወድቅ ነገር ካለ ማንሳት የሚል ፍላጎቱን ሊያሳካ የዘወትር የትርምስ ነጋሪት በመጎሰም ውዥንብር የመፍጠር ተግባሩን አጠናክሮ ቀጥሏል።*

*ልማታዊ አማራጭ መንገዱ ይቻላል በሚል ወኔ በራስ የውስጥ አቅም የሚገነባ፣ ከአፍሪካ በዓይነቱ አንደኛ የሆነ፣ ከዓለም ኢትዮጵያን በስድስተኛ ደረጃ ላይ የሚያስቀምጥ 6000 ሜጋዋት የኤሌክትሪክ ኃይል የሚያመነጨውን የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ፕሮጀክትን አስገኝቷል፡፡*

*ይህ የዚህ ትውልድ ገድልና ኩራት ነው፡፡ ይህ የዕድገት አስተሳሰብና አማራጭ መንገዱ ትሩፋት ነው፡፡*

*የአንድ ትውልድ ታሪክ አካል መሆን መቻል በእድለኝነትም ጭምር የሚገኝ ነው፡፡ ትልቅ ታሪክ የመስራት ዕድል አግኝቶ የሚያልፍ ትውልድ ብዙ አይደለም፡፡ እስከአሁን ዓለም ተናግሮለት ያልጠገበው የእኛም የመላው አፍሪካም ኩራት የሆነው የአድዋ ድል በዚያን ጊዜ በነበረው ዕድለኛ ትውልድ አንድ ጊዜ ብቻ የተሰራ ታሪክ ነውና፡፡*

*በማንቋሸሽና በማጥላላት ፖለቲካ ሀገር ሊገነባ አይችልም፡፡ እንዲህ ዓይነት ታሪክ አልተነበበም፡፡ በዚህ አይነት አፍራሽ ተግባር የተሰማሩ ሰዎቻችን ይህን የሚያደርጉበት መናኛ ግላዊ ስሜት እንዳላቸው አያጠራጥርም፡፡  ነገር ግን ለማይረባ የግል ስሜት በሀገር ልማትና ዕድገት ጉዳይ ላይ በግለፅ በአደባባይ ጋሬጣ ለመሆን መንቀሳቀስ መቼም ቢሆን ይቅር ሊባል የማይችል አንድ የታሪክ ጠባሳ ነው፡፡*

*በሐሰትና  በውዥንብር ፈጠራ ሙያ ተክነው የሚያላዝኑት እነዚህ ግለሰቦችና ቡድኖች የያዙት መንገድ የትም ሊያደርሳቸው እንዳልቻለ ታይቷል፡፡  በመረጡት መንገድ ጉዞ ከጀመሩ በርካታ ዓመታት የተቆጠሩ ቢሆንም በሚቻላቸው አቅም ሁሉ እንቅፋት ለመሆን ከመፍጨርጨር ባሻገር  ለዚህች ሀገር ሠላም ወይም እድገት ጠብ የሚል ነገር እንዳላመጡ እኛ ብቻ ሳንሆን እነሱም ያውቁታል፡፡ ዛሬም ከተነሱበት ሆነው ግን በባዶ ጨኸትና እንቅፋትነታቸው ቀጥለዋል፡፡*

*ዋልድባ ታረሰ፣ ዝቋላ ተቃጠለ፣ ስካይፒ ተከለከለ፣   አማራ ተፈናቀለ፣ ጋምቤላ ተሸጠ፣ መጅሊስ ፈረሰ . . . ወዘተ. ከሚሉት ጀምሮ እስከቅርብ ጊዜዎቹ ልብወለዶች ታሪኮች  ስንት ጉዳይ ተነሳ?*

*ከእነዚህ ጉዳዮች ምን ያህሎቹ እውነትነትና ሚዛናዊነት የነበራቸው ነበሩ? ፍርዱን ለጨለምተኞቹ ለራሳቸውና ለእያንዳንዳችን ህሊና እንተወው፡፡*

*ከእነዚህ ጉዳዮች ሁሉ በስተጀርባ የነበረው የአቀንቃኞቹ ምኞትና ፍላጎት ምን ነበር?  እውን ሀገራዊ ስሜት?*

*በስተጀርባ ያለው ድብቅ ፍላጎት ግልፅ ነው፡፡ ግርግር ለሌባ ያመቻል እንዲባል የኢትዮጵያ ህዝብ እንደ ቱኒዚያ ወይም ግብፅ  ወይም ሶሪያ ወደለየለት ብጥብጥና ትርምስ ገብቶ ከዚያ ሊገኝ የሚችል ትርፍ ካለ ተጠቃሚ መሆን ነው፡፡ አለቀ፡፡*

*ሀገራችን ኢትዮጵያ በሁላችን ልብ ውስጥ አለች፡፡ ዛሬም ነገም ወደፊትም ለዘለዓለም ትኖራለች፡፡ እኛም ልጆቿ በማንም የሀሰት ውዥንብር ሳንደናቀፍ በሚያልፍ የህይወት ዘመናችን የማያለፍ ታሪክ ለመስራት ከቆሙት ጋር ተሰልፈን ታሪክ ሠርተን እናልፋለን፡፡*

*መንገዳቻችን እናስተካክል፣ ልጓም በሌለው ፈረስ የሚደረገው ግልቢያ መጨረሻው ገደል ነው፡፡*

*ውሾች ይጮሃሉ ግመሉ ጉዞውን ቀጥሏል፡፡*

*ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!*

*ቸር እንሰንብት፡፡*